ህዳር 11 2015
4/0051/16

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጉምሩክ ኮሚሽን ቁጥር 1
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Customs Commission No. 1

በአባሪው ለተዘረዘሩት የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ
<u>በያሉበት</u>

ጉዳዩ፡- <u>ላልተወሰነ ጊዜ የውጭ ምንዛሪ እንዳይፈቀድ ክልከላ የተደረገባቸው ተሽከርካሪዎችን ይመለከታል</u>፤

የገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር ክሂገ1/7/252 ቀን 04/02/2015 በተጻፈ ደብዳቤ ላልተወሰነ ጊዜ በባንክ በኩል የውጭ ምንዛሪ የማይፈቀድላቸውን ዕቃዎች ዝርዝር የታሪፍ ቁጥራቸውን ለይቶ ማሳወቁን ተከትሎ ከኮሚሽኑ በቁጥር 4/0332/15 ጥቅምት 09 ቀን 2015 በተጻፈ ደብዳቤ ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተላለፈው ውሳኔ ተፈጻሚ እንዲደረግ፤ እንዲሁም ከኮሚሽኑ በቁጥር 4/0333/15 ጥቅምት 09 ቀን 2015 በተጻፈ ደብዳቤ በጉምሩክ ደንብ ቁጥር 518/2014 ከተፈቀደላቸው ተመላሽ ኢትዮጵያዊያንና በዓለም አቀፍ ስምምነት መሠረት ተሽከርካሪን ጨምሮ ያለውጭ ምንዛሪ ፈቃድ ዕቃ ወደ አገር የማስገባት መብት ካላቸው ዓለም አቀፍ ድርጅቶች እና ግለሰቦች በስተቀር ከላይ የገንዘብ ሚኒስቴር በባንክ በኩል የውጭ ምንዛሪ እንዳይፈቀድላቸው የታሪፍ ቁጥራቸውን ለይቶ የላካቸው ዕቃዎች ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ ፈቃድ /በፍራንኮቫሉታ/ ወደ አገር እንዳይገቡ መከልከሉ ይታወቃል።

ከላይ በተገለፀው አግባብ የውጭ ምንዛሪ ክልከላ የተደረገባቸው ተሽከርካሪዎች ከክልከላ በፊት የተሰጠ የቆዩ የባንክ ፈቃድን በባንኮች በኩል በማራዘም እና በስመ ተመላሽ ኢትዮጵያውያን ስም ተሽከርካሪዎች በብዛት ወደ አገር እየገቡ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል። ስለሆነም በገንዘብ ሚኒስቴር ላልተወሰነ ጊዜ የውጭ ምንዛሪ ክልከላ የተደረገባቸው ተሽከርካሪዎች በማናቸውም አስመጪ፣ ተመላሽ ኢትዮጵያዊያን እና ሌሎች ስም በተራዘመም ይሁን በአዲስ መልክ በተሰጠ የባንክ ፈቃድ ወይም በፍራንኮ ቫሉታ የክፍያ ዘዴዎች በመልቲ ሞዳልም ይሁን በዩኒ ሞዳል ትራንስፖርት ስርዓት ወደ ሀገር ማስገባት በጥብቅ የተከለከለ መሆኑን እያሳወቅ ይህን ውሳኔ በመተላለፍ የውጭ ምንዛሪ ክልከላ የተደረገባቸውን ተሽከርካሪዎች ወደ ሀገር ማስገባት ወይም እንዲገቡ መፍቀድ በህግ የሚያስጠይቅ መሆኑን አሳውቃለሁ።

ከሠላምታ ጋር

ቃበታ ሁርሳ
የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን
ኮሚሽነር

<u>አባሪ</u>፡- 05 ገጽ
<u>ግልባጭ</u>፤
- ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ የገንዘብ ሚኒስቴር
- ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
- <u>አዲስ አበባ</u>
- ለኮሚሽን ጽ/ቤት
- ለጉምሩክ ኦፕሬሽን ዘርፍ
- ለህግ ተገዥነት ዘርፍ
- ለኢንተለጀንስ ዳይሬክቶሬት
- ለገቢ ዕቃ አወጣጥ ዳይሬክቶሬት
- ለታሪፍ ምደባና ስሪት አገር አወሳሰን ዳይሬክቶሬት
- ለጉምሩክ አቤቱታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት
- ለተቋማዊ ስጋት ስራ አመራርና ስነ-ምግባር ዳይሬክቶሬት

<u>ጉምሩክ ኮሚሽን</u>

- ለአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሞጆ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዳማ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለድሬዳዋ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለመቀሌ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
- ለኮምቦልቻ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለባህርዳር ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሀዋሳ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሞያሌ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅግጅጋ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅማ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሠመራ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለእዋሽ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጋላፊ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአሶሳ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅቡቲ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት
- ለታጁራ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት

<u>በያሉበት</u>

መንግስት ለተወሰኑ የዕቃ ዓይነቶች በባንክ በኩል የውጭ ምንዛሪ እንዳይፈቀድ ባስተላለፈው ውሳኔ መሠረት እንዲሁም ይህንኑ ውሳኔ ተከትሎ ለዕቃዎቹ በፍራንኮቫሉታ አገልግሎት እንዳይሰጥ ከኮሚሽኑ መገለጹን ተከትሎ የጉምሩክ ሥነ-ስርዓት ያልተፈጸመባቸው ተሽከርካሪዎች መረጃ፤

ተ.ቁ	የጉ/ቅ/ጽ/ቤት	አስመጪ	የክፍያ ዓይነት (የባንክ ፈቃድ /ፍራንኮቫሉታ)	የባንክ ፈቃድ የተሰጠበት ቀን	ተሽከርካሪውን ወደ ሀገር ለማስገባት ጥያቄ ያቀረበበት ምክንያት /የመኪና አስመጪ፣ ኢንቨስትመንት፣ እርዳታ፣ በተመላሽ...../	ተሽከርካሪው የሚገኝበት (ሀገር ውስጥ የገባ /ያልገባ)	የጉምሩክ ስነ-ስርዓት በመፈጸም ሂደት ላይ ከሆነ ያለበት ደረጃ	የተሽከርካሪ ብዛት	በጉምሩክ ዲክላራሲዮን የተመዘገበ ከሆነ ዲክላራሲዮን ም ቁጥር	ምርመራ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጉምሩክ ኮሚሽን

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
CUSTOMS COMMISSION

ቁጥር/ Ref.No. 4/0332/15
ቀን/Date ግንቦት 09 2015

የጉምሩክ ስነ-ስርዓት ለሚፈፀምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ

በያሉበት

ጉዳዩ፡- ላልተወሰነ ጊዜ የውጭ ምንዛሪ የማይፈቀድላቸውን ዕቃዎች ስለማሳወቅ።

መንግስት በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚታየው የኢኮኖሚ ችግር በተለይም የሸቀጦች ዋጋ ንረት በአገራችንም ጫና እየፈጠረ በመሆኑ ጫናውን ለመቀነስ የተለያዩ የፊስካል፤ የገንዘብና ሌሎች አስተዳደራዊ እርምጃዎች መውሰዱን በመጥቀስ የተወሰዱ እርምጃዎች ይበልጥ ውጤታማ ለማድረግ ላልተወሰነ ጊዜ የውጭ ምንዛሪ የማይፈቀድላቸው ዕቃዎች ዝርዝር የማክሮ ኮሚቴ በሰጠው አቅጣጫ መሰረት የኢ.ፌ.ድ.ሪ የገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር ክሃገ1/7/252 ጥቅምት 04 ቀን 2015 ዓ.ም ለብሔራዊ ባንክ ሲያሳውቅ በግልባጭ ለኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን አሳውቋል።

ስለሆነም የገንዘብ ሚኒስቴር ዝርዝራቸው ከነታሪፍ ቁጥራቸው ገልያ የላካቸው ዕቃዎች ላይ ከጥቅምት 04 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ ከየትኛውም ባንክ በሚሰጥ የባንክ ፈቃድ የጉምሩክ አገልግሎት እንዳይሰጥ ተገቢው ጥንቃቄ እንዲደረግ እያሳወቅኩ፤ ተፈቅዶ የቀረበ የባንክ ፈቃድ ሲያጋጥም የፈቀደውን ባንክ እና ሌሎች ተያያዥ መረጃዎች ተይዘው ለኮሚሽን ጽ/ቤት ሪፖርት እንዲቀርብ በጥብቅ እያሳሰብኩ፤ ከገንዘብ ሚኒስቴር የተላከውን ውሳኔ 03 ገጽ ለአፈፃፀም ልከናል።

በአክብሮት ሰላምታ ጋር

ሙርሳ
ኮሚሽነር

ግልባጭ//

- ለኮሚሽን ጽ/ቤት
- ለኦፕሬሽን ዘርፍ
- ለህግ ተገዥነት ዘርፍ

ጉ/ኮሚሽን፤

ስልክ/Tel:- +251 116 67 54 58
:- +251 116 62 98 19
Email: hocrecordopr@gmail.com
Website:- www.ecc.gov.et
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የግንዘብ ሚኒስቴር

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

MINISTRY OF FINANCE

ቁጥር ፍሄገ/ት/፲፱፭
Ref. No.
ቀን ፬፯/፬፫/፳፬፲፭
Date

ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- ላልተወሰነ ጊዜ የውጭ ምንዛሬ የማይፈቀድላቸው ዝርዝር መላክን ይመለከታል፤

መንግስት በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚታየው የኢኮኖሚ ችግር በሀገራችንም ጫና እየፈጠረ በመሆኑ፡ በተለይም የዋጋ ንረት በህብረተሰቡ ሊያደርስ የሚችለው ጫና ለመቀነስ ሲባል የተላያዩ የፊስካል፣ የገንዘብ እና ሌሎች ክስተዳደራዊ እርመጃዎች መውሰዱ ይታወሳል። የተወሰዱ እርምጃዎች ይበልጥ ውጤታማ ለማድረግ በተለይም የውጭ ምንዛሬ ለመሰረታዊ የምግብ ሸቀጦች፣ ለመድሀኒትና የህክምና መሳሪያዎች፣ ከውጭ ገብተው በአገር ውስጥ እሴት ተጨምሮባቸው ገበ. ምርቶችን ለመተካት የሚውሉ ምርቶች ለማምረት የሚውሉ ግብዓቶች፣ የካፒታል ዕቃዎች ወዘተ ለማስገባት ጥቅም እንዲውል ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

ስለሆነም የማክሮ ኮሚቴ በሰጠው አቅጣጫ መሰረት ላልተወሰነ ጊዜ የውጭ ምንዛሬ የማይፈቀድላቸው ዝርዝር ከነጉምሩክ ታሪፍ ቁጥራቸው ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን መላካችንን እየገለፅን፣ ባንኩ ኮሚቴው በሰጠው አቅጣጫ መሰረት አስፈላጊውን እንዲያደርግ አናሳስባለን።

ከሠላምታ ጋር

ሰመረች ሰዋስው
ሚኒስቴር ዴኤታ

ግልባጭ፡-

- ለንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር
- ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
- ለገቢዎች ሚኒስቴር
- ለጉምሩክ ኮሚሽን
  አዲስ አበባ

Ethiopian Customs Commission Records Documentation No.1

Based on Import Data of 2014 Ethiopian Budget year (1USD = 50Br)			
No	Tariff Code	Product Description	
1	1704	Chewing Gum and Sugar Convectionery	ከረሜላዎች፣ ማስቲካዎችና ሌሎች ጣፋጭ ዝግጅቶች
2	1806 except 18062010	Checolate	ቸኮሌት
3	1905	Sweet Biscuts and Waffles	ብስኩቶችና ዋፊሮች
4	2009	Fruit Juices & canned fruits	የፍራፍሬ ጭማቂና የታሸጉ ፍራፍሬዎች
		Jam, Vimto, Potato chips, Tomato paste	ከፍራፍሬ የተዘጋጁ ጃሞች፣ የድንች ጥብሶች፣
5	22021000	water including Mineral Water፣Soft drninks and other non-alcholic drinks	የታሸጉ ውሃዎች,ለስላሳ መጠጦችና አልኮል የሌላቸው መጠጦች
6	Chapter 22	Wihisky, wine, Beer and all other alcholic drinks	ውስኪ፣ ወይን፣ቢራና ለሎች አልኮል መጠጦች በሙሉ
7	2402,2403, 2404	Cigarettes and Substitutes	ሲጋራ
8	3303	Perfumes and toilet waters	ሽቶዎችና ቶይሌት ዋተርስ
9	33041000, 33042000, 33043000	Make up Preparations	የውበት ወይም የመከላከያ ዝግጅቶች፣
10	3401	Soaps	ሳሙናዎች
11	3604	Fireworks	ርችቶች
12	4202	Bags and Wallets	ቦርሳና ዋሌቶች
13	4909	Post Cards and Similar Cards	የተጋላጭ ስዕላዊ መግለጫ ያላቸው ካርዶች፣
14	4910	Calendars	የቀን መቁጠሪያ ካሌንደሮች፣
15	49119190	Picturess including wall picture	ስዕሎች የግድግዳ ሥዕሎች ጨምሮ
17	6504 & 6505	Hats and Headgears	ባርኔጣዎችና ኮፍያዎች
18	6702	Artificial Flowers	አርቲፊሻል አበባዎች
19	6704	Human and Artificial hairs	የሰውና አርቲፊሻል ጸጉሮች፣
20	Chapter 71except Legal Tender Coins	Artificial Jewellers	አርቲፊሻል ጌጣጌጦች
21	8703	Complet build up/CBU/ Automobiles and Three Wheelers /except electric Motor vehicles/	የተገጣጠመ የቤት አውቶሞቢል እና ባለሶስት እግር ተሽከርካሪዎች /በኤሌክትሪክ ሞተር የሚሰሩትን ሳይጨምር/
22	8711	Complet Build up/CBU/ Motorcycles/except electric Motor vehicles/	የተገጣጠመ ሞተር ሳይክሎች /በኤሌክትሪክ ሞተር የሚሰሩትን ሳይጨምር/

Ethiopian Customs Commission Records Documentation No.1
Ethiopian Customs Commission Records Documentation No.1

Based on Import Data of 2014 Ethiopian Budget year (1USD = 50Br)			
23	8712	Bicycles	ሳይክሎች
24	9401 & 9403	Household and Office Furnitures except specially designed chairs	በታሪፍ ቁጥር 9401 እስከ 9403 የሚመደቡ የቤትና የቢሮ ዕቃዎች
25	25.01	Table salts	የገበታ ጨው
26	chapter 95	Different games	የተለያዩ መጫወቻ እቃዎች
27	chapter 91	Hand watches, table and wall clocks	የእጅ፣ የጠረጴዛና የግድግዳ ሰዓቶች
28	66 01 & 6602	Umbrella	ዣንጥላዎች
29	chapter 57	Carpets	ምንጣፎች
30	1601	pork luncheon meat	የአሳማ ስጋዎች
31	1602	chicken lunchenon meat	የዶሮ ስጋዎች
32	1604	Tuna, sardins and other sea foods	ቱናዎች፣ ሰርዲኖችና ሌሎች የአሳ ምርቶች
33	chapter 19 & 21	Packed foods preparation except milk and praparation for infant or young children	ከህፃናት አልሚ ምግቦችና ወተቶች በስተቀር የተለያዩ የታሸጉ ምግቦች
34	6911-6914	Ceramics and porclin kitchen wares	ከሴራሚክስና ፖርስሊን የተዘጋጁ የቤት እቃዎች
35	9613.	Gas lighter	ጋዝ ላይተር
36	9615	Hair pin, clip, grips, roller, bow,band,pony tail,tiyara	የተለያዩ የጸጉር ጌጣጌጦች
37	96180000	Mannequin	ልብስ ማሳያ አሻንጉሊቶች
38	7013	Glass beer mug, wine, alcohol, ash tray, vase, frame	ከብርጭቆ የተዘጋጁ የመጠጥ መጠጫ እቃዎች፣የስጋራ መተርከሻዎች፣የአበባ መያዣና ተመሳሳይ እቃዎች

Ethiopian Customs Commission
Records Documentation No.1

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጉምሩክ ኮሚሽን
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
CUSTOMS COMMISSION

ቁጥር/ Ref.No. 4/0333/15
ቀን/Date ~~ጥቅምት~~ 0 9 2015

የጉምሩክ ስነ-ስርዓት ለሚፈፀምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ

<u>በያሉበት</u>

ጉዳዩ፡- <u>የፍራንኮ ቫሉታ አፈቃቀድን ይመለከታል፡፡</u>

መንግስት በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚታየው የኢኮኖሚ ችግር በተለይም የሸቀጦች ዋጋ ንረት በአገራችንም ጫና እየፈጠረ በመሆኑ ጫናውን ለመቀነስ የተለያዩ የፊስካል፤ የገንዘብና ሌሎች አስተዳደራዊ እርምጃዎች መውሰዱን በመጥቀስ የተወሰዱ እርምጃዎች ይበልጥ ውጤታማ ለማድረግ ላልተወሰነ ጊዜ የውጭ ምንዛሪ የማይፈቀድላቸው ዕቃዎች ዝርዝር የማክሮ ኮሚቴ በሰጠው አቅጣጫ መሰረት የኢ.ፌ.ድ.ሪ የገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር ክሂ.ገ1/7/252 ጥቅምት 04 ቀን 2015 ዓ.ም ለብሔራዊ ባንክ ሲያሳውቅ በግልባጭ ለኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን አሳውቋል፡፡

ስለሆነም በጉምሩክ ደንብ ቁጥር 518/2014 ከተፈቀደላቸው ተመላሽ ኢትዮጵያውያንና በዓለም ዓቀፍ ስምምነት መሰረት ተሽከርካሪን ጨምሮ ያለውጭ ምንዛሪ ዕቃ ወደ አገር የማስገባት መብት ካላቸው ዓለም አቀፍ ድርጅቶች እና ግለሰቦች በስተቀር የገንዘብ ሚኒስቴር ዝርዝራቸው ከነታሪፍ ቁጥራቸው ገልፆ የላካቸው ዕቃዎች ያለውጭ ምንዛሪ ፈቃድ /ፍራንኮ ቫሉታ/ ወደ አገር እንዲገቡ መፍቀድ የተከለከለ መሆኑ ታውቆ ጥንቃቄ እንዲደረግ በጥብቅ አሳውቃለሁ፡፡

ከሰላምታ ጋር

ደበሌ ታበታ ሁርሳ
የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር

<u>ግልባጭ</u>//

- ለኮሚሽን ጽ/ቤት
- ለኦፕሬሽን ዘርፍ
- ለህግ ተገዥነት ዘርፍ

<u>ጉ/ኮሚሽን</u>

ስልክ/Tel:- +251 116 67 54 58
:- +251 116 62 98 19
Email: hocrecordopr@gmail.com
Website:- www.ecc.gov.et
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia